Washington State Department of Labor & Industries

የሥራ ደህንነት እና ጤና ህግ

አሠሪዎች ይህን ማስታወቂያ ሠራተኞቻቸው ሊያነቡት በሚችሉበት ቦታ መለጠፍ አለባቸው።

ሁሉም ሠራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የሥራ ቦታ የማግኘት መብት አላቸው።

ሠራተኞች — ቀጣሪያችሁ በሥራ ላይ ከሚያጋጥሙዋችሁ አደጋዎች መጠበቅ፣ ስለእነሱ ለእናንተ መንገር እና ስልጠና መስጠት አለበት።

የሚከተሉትን ለማድረግ መብት አላችሁ፦

- ስለ የሥራ ቦታ አደጋዎች ለቀጣሪያችሁ ወይም ለ L&I (ሠራተኛ እና ኢንዱስትሪዎች) አሳውቁ። ሰማችሁን በሚስጥር እንዲይዝ L&I ን መጠየቅ ትችላላችሁ።
- አደገኛ ወይም ጤናማ ያልሆኑ ሁኔታዎች አሉ ብላችሁ ካመናችሁ በሚሠሩበት ቦታ የ L&I ፍተሻ እንዲደረግ ጠይቁ። እናንተ ወይም የሠራተኛ ተወካያችሁ ደመወዝ ወይም ጥቅማጥቅሞችን ሳያጡ በፍተሻው ውስጥ ሊጸተፉ ትችላላችሁ።
- ለመርዛማ እና ጎጂ ንጥረ ነገሮች ወይም ሁኔታዎች የመጋለጥ መዛግብቶቻችሁን ጨምሮ የህክምና መዝገቦቻችሁን ቅጂዎች አግኙ።
- ቀጣሪዎ የደህንነት ቅሬታ ሰላቀረቡ፣ በፍተሻ ላይ ወይም ከደህንነት ጋር በተያያዘ ሌላ እንቅስቃሴ ላይ ሰለተሳተፉ አባሮኛል፣ ወይም የአጸፋ እርምጃ ወሰዶብኛል ወይም አድሎ አድርጎብኛል ብለው ካመኑ፣ በ 90 ቀናት ውስጥ ለ L&I ቅሬታ ያቅርቡ።

ህጉ በድርጊቶችዎ እና በሥራው ስነምግባር ላይ የሚተገበሩት የሥራ ቦታ ደህንነት እና ጤና ደንቦችን እንዲከተሉ ያስገድዳል።

አሠሪዎች — በሥራው ላይ ሠራተኞችን ለመጠበቅ ህጋዊ ግዴታ አለባችሁ።

አሠሪዎች በሠራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትሉ ከሚችሉ አደጋዎች ነጻ የሆኑ የሥራ ቦታዎችን መስጠት አለባቸው።

መውሰድ ያለባችሁ እርምጃዎች፦

- የጽሁፍ የአደጋ መከላከል ዕቅድ (እንዲሁም አደጋ መከላከል ዕቅድ (Accident Prevention Plan, APP) ወይም የደህንነት ፕሮግራም ተብሎም የሚጠራውን) ማዘጋጀት እና መተግበርን ጨምሮ፣ በንግድ ሥራችሁ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑትን ሁሉንም የሥራ ቦታ የደህንነት እና ጤና ህጎችን አክብሩ።
- ለሠራተኞቻችሁ መብቶቻቸውን እና ግዴታዎቻቸውን ለማሳወቅ ይህንን ማስታወቂያ ለጥፉ።
- ከሥራ ምደባ በፊት ሠራተኞች አደገኛ ተጋላጭነቶችን እንዴት መከላከል እንደሚችሉ አሠለጥኑ እና አስፈላጊውን የግል መከላከያ መሳሪያዎችን ያለምንም ወጪ አቅርቡላቸው።
- የሠራተኛ ተወካይ ደመወዝ ወይም ጥቅማጥቅሞችን ሳያጣ በ L&I ደህንነት/ጤና ቁጥጥር ላይ እንዲሳተፍ ፍቀዱ። የ L&I ተቆጣጣሪው ከበርካታ ሠራተኞች ጋር በሚሰጥር መነጋገር ይችላል።
- ለደህንነት እና/ወይም ለጤና ጥሰት ሰማችሁ ከተጠቀሰ፣ ጥቅሱን ቅዳሜ እና እሁድን እንዲሁም በዓላትን ሳያካትት ጥሰቱ በተፈፀመበት ቦታ ወይም አቅራቢያ ላይ ቢያንስ ለሰባት የሥራ ቀናት በግልፅ ማሳየት አለባችሁ። ሁሉም ጥሰቶች እስኪሰተካከሉ ድረስ ተለጥፎ መቀመጥ አለበት።
- በጥቅሱ ላይ የሚፈቀደው ጊዜ ምክንያታዊ አይደለም ብለው ካመኑ፣ የጥሰት ማሰተካከያ ቀን ይግባኝ ያሰገቡ።

ቅሬታ በማቅረቡ ወይም በቁጥጥር ፍተሻ፣ በምርመራ ወይም በመክፈቻ ወይም በመዝጊያ ስብሰባ ላይ በመሳተፉ ማንኛውንም ሠራተኛ ማባረር ወይም አጸፋ መመለስ ህገወጥ ነው።

አሠሪዎች ሁሉንም ሞት፣ ሆስፒታል ተኝቶ መታከምን፣ መቆረጦችን ወይም የዓይን ማጣትን ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

ማንኛውንም ከሥራ ጋር የተያያዘ ሞት ወይም ሆስፒታል ተኝቶ መታከምን በ 8 ሰዓታት ውስጥ ለ L&I የሥራ ደህንነት እና ጤና ክፍል (Division of Occupational Safety and Health, DOSH) ሪፖርት አድርጉ።

ማንኛውም ከሥራ ጋር የተያያዘ ያልሆነ እና ሆስፒታል ሳይተኙ የተቆረጡትን ወይም ዓይን ማጣትን በ 24 ሰዓት ውስጥ ለ DOSH አሳውቁ።

ለማንኛውም ከሥራ ጋር የተያያዘ ሞት፣ ሆስፒታል ተኝቶ መታከም፣ መቆረጥ ወይም አይን ማጣት፣ የሚከተለውን መረጃ ለ DOSH ሪፖርት ማድረግ አለባችሁ።

- የአሠሪ ተጠሪ እና ስልክ ቁጥር።
- የንግድ ስም።
- አድራሻ እና ከሥራ ጋር የተያያዘው አደጋ የተከሰተበት ቦታ።
- የክስተቱ ቀን እና ሰዓት።
- የሠራተኞች ብዛት እና ስማቸው።
- ስለተፈጠረው ነገር አጭር መግለጫ።

የት ሪፖርት እንደሚደረግ፦

- ማንኛውም የአካባቢ L&I ቢሮ ወይም
- 1-800-423-7233፣ 1 ን ይጫኑ (24/7 ይገኛል)

ይህ ፖስተር ከ L&I በነጻ በ **Lni.wa.gov/RequiredPosters** ላይ ይገኛል።

ነፃ እርዳታ ከሥራ ደህንነት እና ጤና ክፍል (DOSH)

- ሰልጠና እና ግብዓቶች ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታዎችን ለማበረታታት።
- አሠሪዎች አደጋዎችን እንዲለዩ እና እንዲያስተካክሉ ለማገዝ በቦታው ላይ የሚሰጥ ምክክር እና የሠራተኞቻችሁን የካሳ ዋጋዎችን ለመቀነስ የሚደረግ የአደጋ አስተዳደር ድጋፍ።

Division of Occupational Safety and Health

Lni.wa.gov/go/F416-081-201 | 1-800-423-7233

በሚጠየቅበት ጊዜ፣ የቋንቋ እገዛ እና የአካል ወይም የአዕምሮ እክሎች ላለባቸው ሰዎች የሚሆኑ ቅርጸቶች ይገኛሉ። በ 1-800-547-8367 ላይ ደውሉ። የ TDD ተጠቃሚዎች፣ በ 711 ደውሉ። L&I የእኩል እድል ቀጣሪ ነው።

PUBLICATION F416-081-201 (Amharic) [07-2025]